EthioLion

# “ አማራ፡ ‘የተቀጣ ዘ-ብሄረ አይሁድ’ ”

የጐንቻው!



የኳተነው ቀልቤ ከቀዬ ሲለይ፤
ነፍሴ እንደጨነቃት አንጋጥጨ ባይ፤
አልታዩኝ አለ የአገሬ ሰማይ፤
ዓይኔን እንባ ሞላው በጨረር ጸሃይ፤
የምድራችን ‘ጌቶች’ ክልል ይሆን ወይ፤
**ቀና ብዬ እንዳልሄድ አዘቅዝቆ እሚያይ።**

**ማነኝ እኰ አሉ እኔ? አማራ አሉኝ፤አይሁድ፤**
በጐጥ፤በቀነኞች ታድኜ እምሳደድ፤
መጤ፤ስደተኛ፤ፈላሻ አገር የለሽ፤
ሃያ ዘመን ጦሴን ፍዳ ይዤ እመሸሽ፤
ምነ? አትማልጂ ጀምበር በቀን አረፋፍደሽ፤
እገባበት የለኝ፤ አድርበት ሲመሻሽ፤
**መጠጊያ ነፈጉኝ ለአንዱ እግዜር እንግዳሽ።**



ካቴድራል ስላሴ ታቦቷም የለሽ፤
አረም በቅሎብሻል ‘**አድዋ**’ ውጦሽ፤
በታጠቁ ካድሬ ደንቀራ አቡንሽ፤
አገር ደጀ ሰላም ‘አባ አገር ምዶሽ’፤
አሳር ቁም አስቀጡኝ ቂመኛው ‘ንግስሽ’፤
ጥግ ድንኳን ገፈው ‘ቀሳውስቶችሽ’፤
**አንቺ እናት ኢትዮጵያ ይፍረድ ሰንደቅሽ።**

‘ሺህ በላው፤ሺህ ፈራው’ መለስ አጋሰስ፤
ቁንጣን ተጨናንቆ መዳፍ እሚነክስ፤
ዘር በላ አይጠመጐጥ አውድማ ነስቶኝ፤
የእሱን በምድር ቀብሮ ከአፌ እሚቀማኝ፤
ባንዳ የደቀለው ባድ’ማ ነቅሎኝ፤
**እርስት ባላአገሩን ለማኝ አረገኝ።**



ልጅ አበሳ አዝዬ በራብ ጥማት ዝዬ፤
እንከራተታለሁ ግዞት ነው ኑሮዬ፤
መንግስት አለ ብዬ ዳኛ አለ በአገሩ፤
አቤት ብል ከደጃፍ ብሰጣ ከበሩ፤
ተናካሽ ውሻቸው፤ክፍ ወታደሩ፤
ቂመኛ ጥርሻቸው አጥንት የሚሰብሩ፤
ሥጋ ደጅ መንሻቸው በደም የከበሩ፤
ስሜን ክብሬን ገፈው ረግጠው ካፈሩ፤
ንጉሥ ጃዝ ያሏቸው ‘ብአዴን’፤ ባእዳን ጅቦች ቢጠራሩ፤
የተጋጋጠውን ለቅመው የሚቀብሩ፤
‘ትውልድ የሚያጠዱ’ ካገር ከመንደሩ፤
**ጫኑኝ በጨለማ እየወረወሩ፤እየገፈተሩ።**




ይግባኝ የለም በምድር በሰማይ ችሎት፤
መነሻየስ የት ነው? የእትብቴ ቋሪት፤
እኰ መደረሻየስ? የዓለሜ ግብዓት፤
መሬት ከተፋችኝ መቀመቅ ግዞት፤
እንዳትቆምብኝ፤እንዳልቆምባት፤
**<u>ደግሞ</u> እስከወዳኛው የዓለም ፍርድ ጥናት።**

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

ምድር እንድነካ 'ጌቶቹ' አይፈቅዱም፤
አቃጥለው ሲያነዱ ከሰሉም ጢሱም፤
በውስጤ ተቀብሮ ውጭ አይታይም፤
ተበትኜ እንድተን ስውር፤እንደ ጉም፤
**የ 'ቀነኞች' ሴራ አውድሞ መውደም።**

**ስም ቀብቶ አለ ስሜ መጥፎ እሚከረፍ፤**
ወግቶ ያስወጋኛል ቁስሌን እያሰፋ፤
ዛሬ **'ጉራ ፈርዳ'** 'ማጅ ዞን' ገፋኝ፤
ትናንት **'አርባ ጉጉ'** እንዳቃጠለኝ፤
ሃያ ዓመት በሰይፉ እያሳረደኝ፤
ስለቱን በአንገቴ ሲሞርድብኝ፤
ዶማውን በአናቴ ሲቀጠቅጠኝ፤
ምነው አዛኝ ከልካይ አምላክ ያሳጣኝ፤
ስጠቃ እሚመክት ወገን የለለኝ፤
**ምድር ወይስ ሰማይ እኔን የከዱኝ።**

ዘሬን ሳያመክኑት ከንፈ ልሂድ፤
ደመና ለብሼ ዝናብ ነጎድጓድ፤
መብረቅ ከቋጠረው 'የግንቦት በረድ'፤
ቀን ከጫረው 'እሳት' ማዕበል ሰደድ፤
ከተቀጣጠለው እንድንዋሃድ፤
**'ዘር በላ አይጠ መጎጥ' የምሱን በዓመድ፤**
ረድዔቱ እንዲተርፍ ትልቁ 'መአድ'
አገር ሕዝብ ኢትዮጵያ እንዳትዋረድ፤
አማራ፤ኦሮሞ፤ትግራይ አንድ ግንድ፤
ብሄረ ብዙሃን ሰላም እንዲያውርድ፤
**ስደት ግዞት ይቁሞ እንፈቃቀድ።**


# የጎንቻው!

yegonchaw@yahoo.co.uk


- ከትውልድ ሃገራቸውና፤ከቀያቸው፤እየተሳደዱ በየአቅጣጫው ለእልቂት ለተዳረጉት የአማራ ብሄር ተዋላጆች፤ኢትዮጵያያዊን ላይ ለዓለፍት ሃያ ዓመታት በዘረኛው የወያኔ ቡድ ሆን ተብሎ በእቅድ በተቀነባበር የዘር ማጥፋት ዘመቻ በሚካሄድበት የአማራ ብሔር የመታደግ ጥሪ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ በአስቸኳይ እንዲጀምር።
- በአሁኑ ጊዜም ከጊዚያዊ መጠለያ በግዳጅ ተጭነው አድራሻቸው ላልታወቁት ዜጎቻችን የዓለም መሪዎች፤የሰብ ዓዊ መብት ተሚጋቾች እንዲከታተሉት እንዲደረግ፤ከሁሉም በላይ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህን ዓረመኔ የወያኔ ቡድን አስቃቂ ገጽታ በጋህድ እንዲያውቀው እንዲደረግ።

EthioLion.Com